# ሱስ

ሱስ በተደጋጋሚ እና ቋሚ ሊባል በሚቻል መልኩ ለረጅም ጊዜ የሚደረግ እና በአንድ ነገር ላይ አካላዊ፣ ባህርያዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጥገኝነትን የሚያሳይ የአዕምሮ ሕመም ነው።ሰዎች ከተለያዩ ነገሮችበመጠቀምወይም በመጫወት ሱስ ሊይዛቸው ይችላል። በዋነኝነት የሚጠቀሱት የንጥረ ነገር ሱሶች ማለትም እንደ አልኮል፣ጫት፣ሲጋራ፣የተለያዩ አደንዛዥ እና አነቃቂ እፅዋት እንዲሁም መድሃኒቶች ሲሆኑ ከእነዚህ ባልተናነሰ መልኩ ሰዎች እንደቁማር፣ቴክኖሎጂ እና የመሳሰሉ የባህርይ ሱሶችም ከሱስ ይመደባሉ ።

በአገራችን ብሎም በአለማችን የተስፋፋው የሱስ ችግር በአብዛኛው በወጣቶች ላይ ከእድሜያቸው ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮች ሲሆኑ የአካባቢያዊ እና የአቻ ተፅእኖ ምክንያቶች ደግሞ በዋነኝነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ችግሮች ናቸው።

ሰዎች ወደሱስ የሚገቡባቸው ምክንያቶች ለመነቃቃት፣ ከድብርትና ከጭንቀት ስሜት ለመላቀቅ፣ የደስታና የመዝናናት ስሜትን ለመፍጠር፣ሕመምን ለማስታገስ እና ጊዜን ለማሳለፍ የሚሉት ሰዎች በአብዛኛው ሱስ ውስጥ እንዲገቡ የሚያስቀምጧቸው ምክንያቶች ናቸው።

ሱስ ያለበት ሰው የሚያሳያቸው ምልክቶች እንደሚጠቀመው ነገር የሚለያዩ ቢሆኑም ጠቅለል አድርገን ስናያቸው ግን ሱሱን ለመጠቀም ከፍተኛ ጊዜ ማጥፋት፣ለማቆም ወይም ለመቀነስ መቸገር፣አምጣ አምጣ የማለት ስሜት፣ለማቆም ወይም ለመቀነስ በሚሞክርበት ጊዜ የተለያዩ አካላዊ የሆኑ የሕመም ምልክቶችን ማሳየት፣የንጥረ ነገሩን መጠን በየጊዜው መጨመር፣የአካል እና የአዕምሮ ጤና መቃወስ እንደሚያስከትል እያወቁ መጠቀም፣የስራ እና የትምህርት መስተጓጎል፣ሃላፊነቶችን አለመወጣትና ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ መግባት፣ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ እና ከስራ ባልደረባ ጋር ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት ውስጥ መግባት፣ንጥረ ነገሮቹን ተጠቅሞ ሕይወትን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ድርጊቶችን ማከናወን የመሳሰሉት ናቸው።

ማንኛውም አይነት ሱስ ያለበት ሰው ከሱስ መላቀቅ የሚችለው ተገቢው የስነአዕምሮ ሕክምና ክትትል ከተደረገለት እና ከሚያደርገው የሕክምና ክትትል በላይ የራሱ ዝግጁነት እና ቁርጠኝነት ከታከለበት ሙሉ በሙሉ ከሱሰኝነቱ ማገገም እና መላቀቅ ይችላል።

**ምንጭ** ፡- አዲስ አበባ ጤና ሚኒስቴር ጥር 29/ 2016 ዓ.ም (አዲስ አበባ | ጥር 29፣ 2016፤ NBC ETHIOPIA)